
ካብዩ ኣደም



የመጀመሪያው ሰው

All right reserved

© የወጣቱ ተልዕኮ
የወጣቱ ተልዕኮ የኦንላይን እትም 2010
ሰሜን ወሎ ወልድያ

ahmedyesuf29@gmail.com

+251927790323

https://youth-mission.com




የወጣቱ ተልዕኮ

Presented by: Youth-Mission Online Amharic Islamic Books Publishing.



بسم الله الرحمن الرحيم


አሏህ መልአክቶችን ሲያናግራቸው የሰው ልጅ አደምን ልፈጥር ነው አላቸው።



አሏህ አደምን የፈጠረው ከሞቃ ሲሆን የቀረፀው በእጆቹ ነው።

አደም የተፈጠረው ከአላማ ጋር ነው። እሱም አሏህን ብቻ ለመገዛት ነው።






አሏህ የአደምን ነፍስ ወደ እሱ ነፋበት። ነፍሱ አፍንጫው ላይ በደረሰች ጊዜ አስነጠሠው አልሐምዱሊላህ ረቢል አለሚን አለ።


የርሃኩሙሏህ ሲል አሏህ መለሰለት

አሏህ ለአደም የነገሮችን ስም አስተምሮታል። መልአክቶች የነገራቶችን ስም ይነግሩት ይችሉ እንደሁ ጠየቃቸው።

መልአክቶች ስሞቹን አያውቁም። አደም ነገራቸው። ከዚያም መልአክቶች ለአደም እንዲሰግዱ አሏህ አዘዛቸው።

እሱን ለማክበር ለአደም ሰገዱ።ምክኒያቱም ከእነሱ የበለጠ እውቀት አለው።





ኢብሊስ ጅን ነበር።ለአደም እንዲሰግዱ አሏህ ባዘዛቸው ጊዜ እሱ ከመልአክቶች ጋር ነበር። ኢብልስ ግን አልሰግድም አለ።ኢብሊስ ሆይ! እነዚያ ከሰገዱት ጋር የማሰግደው ለምንድን ነው? ሲል ጠየቀው።




ኢብሊስ ሲመልስ እኔ ከእሱ የበለጥኩ ነኝ። እኔን ከእሳት ፈጠርከኝ። እሱን ደግሞ ከጭቃ ፈጠርከው አለ።


ኢብሊስ ኩሩና ትዕቢተኛ ነው። ከአደም (ዐ.ሰ) የበለጠ እንደሆነ ነው ያሰበው።

አሏህን አልታዘዘም፤ ከሃዲም ሆነ። ከዚያ ቀን ጀምሮ ኢብሊስ የሰው ልጆችን ከአሏህ መንገድ ለማስወጣት እና ለማሳሳት ፣ ለማተለል ቃል ገባ።

አደም (ዐ.ሰ) አደም የጀነት አትክልት ቦታ ውስጥ ነበር። አንድ ቀን ሲነቃ ከጎኑ አንዲት ሴት አገኘ። ከአደም የጎን አጥንት አሏህ ፈጠራት። ስሟ ሐዋ ነው።ይህ ስም የተሰጣት ምክኒያቱ ህይወት ካለው ነገር ስለተፈጠረች ነው።

ሐዋ ለአደም ሚስት እንድትሆነው አሏህ ፈጠራት።







አደም እና ሐዋ አብረው የጀነት አትክልት ውስጥ እንዲኖሩ ፣ ደስ ያላቸውን እንዲበሉ አላህ ገራቸው። ነገርግን ያችን ዛፍ እዳትበሉ ብሎ አስጠነቀቃቸው።

አንድ ቀን ኢብሊስ ወደ አደምና ሐዋ መጣና አታለላቸው። ከዚህ ዛፍ ብትበሉ ለዘላለም ትኖራላችሁ አላቸው።

ሆኖም የአሏህን ትዕዛዝ ረሱ። ከዛፏም በሉ።






ከዛፏእንደበለውምስህተታቸውንአወቁ

በጣምአዘኑ፤ ምክኒያቱምአሏህንአልታዘዙም።

አሏህ አደምን ፣ሐዋን እና ኢብሊስን ከጀነት አስወጣቸው። በምድር ላይ እንዲኖሩ እና አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ጠላቶች እንደሆኑም ነገራቸው።


ጀነት እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው አሏህን የታዘዙት እና መልካም ስራዎችን የሰሩት ናቸው።



አሏህ አረህማን (ርህሩህ አዛኝ) ነው። አደምና ሐዋ ምህረት መጠየቅን አስተማራቸው። እንዲህምአለ፡ ጌታችን ሆይ ነፍሳችንን በደልን። በእርግጥ ባትምረን እና ባታዝንልን ከከሳሪዎች እንሆናለን።

(አል-ቁርአን 7፡23)

እናም አሏህ ተውበታቸውን (ንሰሃቸውን) ተቀበላቸው፤ ማራቸውም። ምክኒያቱም አሏህ አተዋብ ነው። ተውበትን (ንሰሃን) ተቀባይ ነው።




رَبَّنَا تَقَبَّلْ مِنَّا إِنَّكَ
أَنْتَ السَّمِيعُ العَلِيمُ

ማንኛውም አይነት ሃሳብ አስተያየት ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወሉልኝ ይችላሉ። የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.com ይጎብኙና መልዕክት ያስቀምጡልን። ጀዛኩሙሉህ ኸይረን ከሲረን!